## *እግዚአብሔር የተወሰኑ ሰዎችን ለመንግሥቱ ሌሎችን ደግሞ ለገሃነም ወስኗል?*

አንዳንድ ወገኖች "የሰው ዕድል ፈንታው ጽዋዕ ተርታው ከጻድቃን ወይም ከኩንኖች መሆን አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተወሰነ ነው" በማለት ይናገራሉ። ለዚህ ቅድመ ውሳኔ /Predestination/ ሐሳባቸውም አስረጅ አድርገው የሚያቀርቧቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች አሏቸው /ሮሜ.9፡11-21፣ ኤፌ.1፡4/። ከዚህም በመነሣት ድኅነት የሚገኘው ከዘመናት በፊትእግዚአብሔር በወሰነው መሠረት እንጂ ሰው በሚፈጽመው ሥራ የማይሰጥ መሆኑን ይናገራሉ። እስኪ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ ጉዳይ ምን ብላ እንደምታስተምርና የእነዚህ ሰዎች አስተምህሮ የሚያመጣው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተፋልሶ ምን እንደሆነ እንመልከት!

## *<u>1.አስቀድሞ ሁሉን ማወቅ ወይስ አስቀድሞ መወሰን?</u>*

እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት እስከ ዓለም ፍጻሜ ሊሆን ያለውን ነገር ምንም ሳይሰወርበት ሁሉን ያውቃል። አንድ ሰው ከቅዱሳን ወገን አልያም ከኃጥአን ወገን እንደሚሆን አስቀድሞ ያውቃል /ሮሜ.8፡28-30/። ሆኖም ግን የተወሰኑትን ለመንግሥተ ሰማያት የተወሰኑትን ደግሞ ለገሃነም ለኩነኔ አልፈጠራቸውም። እንዲህ ቢሆንስ ኖሮ እግዚአብሔር አንድስ እንኳ ይጠፋ ዘንድ እንደማይፈልግ ባለተናገረ ነበር /2ጴጥ.3፡9/፤ የዓለም ሕዝብ በሙሉ ለድኅነት መጥራት ባላስፈለገ ነበር /ማቴ.28፡19፣ ሮሜ.8፡19/፤ ሰዎች ሁሉ ይድኑ እውነትንም ያውቋት ዘንድ ባልወደደ ነበር /1ጢሞ.2፡4/። በመሆኑም ሰው ከእግዚአብሔር በተቀበለው ነጻ ፈቃዱ ተጠቅሞ ወይ ርትዕት በሆነች የሕይወት መንገድ ይጓዛል አሊያም የሞት መንገድ በምትሆን በኃጢአት መንገድ ይሄዳል። ድኅነት ለሁሉም የተሰጠ ቢሆንም የሰው ድኅነቱ በራሱ መሻትና የነጻ ፈቃድ ምርጫ ላይ የተመሠረተ ነው። ሄሬኔዎስ የተባለ አባትም፦ "ጥቂቶች በተፈጥሮ ክፉ ቢሆኑ ሌሎችም መልካም ቢሆኑ መልካሞቹ ስለ መልካምነታቸው መልካም ሠሩ ተብለው ምስጋና የተገባቸው አይሆኑም። ሲፈጠሩ እንዲህ ሆነው ነውና። ክፉዎቹም ስለ ክፋታቸው ነቀፌታን ባላገኛቸው ነበር። ጥንቱንም ሲፈጠሩ እንዲህ ሆነዋልና" ብሏል /Iraneus, Book IV, Chap.37/።

## 2. እግዚአብሔር አያዳላም ፍርዱም ርቱዕ ነው!

እግዚአብሔር የተወሰኑ ሰዎችን ለመንግሥተ ሰማያት ሌሎችን ደግሞ ለገሃነም አስቀድሞ ወስኗል ማለት ክብር ምስጋና ለስም አጠራሩ ይሁንና እግዚአብሔር ያዳላል እንደማለት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን “አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ፣ የጌቶች ጌታ፣ ታላቅ አምላክ፣ ኃያልም፣ የሚያስፈራም፣ በፍርዱም የማያዳላ፣ መማለጃም የማይቀበል ነው” /ዘዳ.10፡17/፤ “እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንደማያዳላ በእውነት አየሁ” /ሐዋ.10፡34/፤ “ከእግዚአብሔር ዋጋችሁን እንደምትቀበሉ ታውቃላችሁ፤ ለክርስቶስ ትገዛላችሁና፤ የሚበድል ግን ፍዳውን ያገኛል እርሱም አያደላለትም” ይላል /ቈላ.3፡23/፡፡

## 3.አስቀድሞ መወሰን አለ ከተባለ ትእዛዛት ለምን ተሰጡ?

እግዚአብሔር የተወሰኑትን ሰዎች ለመንግሥተ ሰማያት የተወሰኑትን ደግሞ ለገሃነም ፈጠረ ከተባለ ሰዎች በአእምሮ ጠባይ መሪነት፣ በሥነ ፍጥረት አስተማሪነት፣ በሕገ ልቡና አዋቂነት መልካም ሥራ መሥራት ሲያቅታቸው በየዘመናቱ ነቢያትን፣ ነገሥታትን፣ ካህናትን እያስነሣ መላኩ (ሎቱ ስብሐትና) ለከንቱ ነውን? ሐዋርያትና ሊቃውንት እንዲሁም ሰባክያን ለትምህርት ለተግሳጽ መላካቸው ምን ፋይዳ አለው /ማቴ.28፡19፣ 2ቆሮ.5፡8/?

## 4. የተወሰኑትን ቀድሞ ለድኅነት ከወሰነ ሥጋዌ አድልዎ ነበረበታ!

አስቀድሞ መወሰን ከሥጋዌው ዓላማ ጋር የሚቆም አይደለም፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸዋትወ መከራን ተቀብሎ የሞተው ለመላው ዓለም እንጂ ለተወሰኑት ሰዎች ብቻ አይደለም፡፡ መጽሐፍ ይህን ሲመሰክር እንዲህ ይላል፡- “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው አንድያ ልጁን ለቤዛ ዓለምና ለካሳ ሰጠ” /ዮሐ.3፡16/፤ “እርሱም የኃጢአታችን ማስተሥርያነው ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም ነገር ግን ለዓለም ሁሉ ኃጢአት እንጂ” /1ዮሐ.2፡2/፤ “ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ” /1ጢሞ.2፡5/፤ “አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ” /2ቆሮ.5፡14/፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮትም፡- “የጽድቅ ልጅ ለሁሉም ተገልጧል፤ ለሁሉም ኑሯል፤

ለሁሉም ሞቶ ተነሥቷል” በማለት ሥጋዌው ለሕዝብም ለአሕዛብም መሆኑን ገልጧል። ምንም እንኳን ድኅነት ለሁሉም የተሰጠ ቢሆንም የመስቀሉ ጠላቶች ሆነው አሻፈረኝ ላሉት ቅጣት ቢያገኛቸው የፈቃድ ምርጫቸው ውጤት ስለሆነ ሓላፊነቱን የሚወስዱ ራሳቸው ናቸው። ለዚህም ነው እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው የሚያስረክበው። ነቢዩ ኢሳይያስም “በመገረፉ ቁስል ተፈወስን” አለ እንጂ “አስቀድሞ ለመንግሥተ ሰማያት የወሰናቸውን በመገረፉ ቁስል ፈወሳቸው” አላለም /ኢሳ.53፡5/። የዕዳ ደብዳቤአችንን የቀደደው የሁላችንም እንጂ ለተወሰኑት ሰዎች ብቻ አይደለም /ቈላ.2፡14/። እንኳንስ ሰዎች ሰይጣንም ለገሃነም የተፈጠረ አይደለም።

## *5. እግዚአብሔር በንስሐ የተመለሱትን ይቅር ማለቱስ?*

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ንስሐን መስጠቱ ኃጢአትን በመውደዱ አይደለም። ሰውን በመውደዱ እንጂ። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ኃጥእ ከክፉ ሥራው ተጸጽቶ ከተመለሰና ንስሐ ከገባ ይቅር እንደሚባል ይናገራል /ሕዝ.33፡14-17፣ ኤር.18፡7-8፣ ሚል.5፡7፣ ያዕ.4፡8/። በራሳቸው ክፉ ምርጫና በኢተነሳሒ ልቡናቸው ምክንያት ብዙዎች የውርደት ዕቃ እንደሆኑ እናውቃለን። ነገር ግን እግዚአብሔር ዘለአለማዊ ቅጣትን አስገኘ አንልም። ንስሐ በሚገባ አንድ ኃጥእ ምክንያት በሰማይ ደስታ እንደሚሆን ነግሮናልና። ከቀደመ ክፉ ግብራቸው ተጸጽተውና ተመልሰው ምሕረትን ያገኙ ብዙ ሰዎች አሉ /2ዜና.33፡1-6/። እንግዲህ እግዚአብሔር የበደለውን በንስሐ ወደ ክብር ዕቃነት የሚመልስ ከሆነ የቅድመ ውሳኔ ትምህርት ተአማኒነት ወዴት አለ? ተወዳጆች ሆይ! መዳናችን ወይም መኰነናችን በእኛ የፈቃድ ምርጫ የሚወሰን መሆኑን ከተመለከትን ዘንዳ ከእንግዲህ ወዲህ ይህን ሐሳብ አንቀበለው።

## *6.ቅድመ ውሳኔ አለ ከተባለ ነጻ ፈቃድ መሰጠቱ ለምንድን ነው?*

መጽሐፍ ቅዱስ በማያሻማና በግልጽ ቋንቋ እንዲህ ይላል፡- “ተመልከት፤ ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን፥ ሞትንና ክፋትን አኑሬአለሁ። በሕይወትም እንድትኖር እንድትባዛም፥ አምላክህም እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባባት ምድር እንዲባርክህ፥ አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ፥ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ ትእዛዙንና ሥርዓቱን ፍርዱንም ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ እኔ አዝዝሃለሁ። ልብህ ግን ቢስት አንተም ባትሰማ፥ ብትታለልም፥ ለሌሎችም አማልክት ብትሰግድ ብታመልካቸውም ፈጽማችሁ እንድትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኋለሁ፤ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ትወርሳት

ዘንድ በምትገባባት ምድር ዘመናችሁን አታስረዝሙም። በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ” /ዘዳ.30፡15-19/፤ “እጅህን በመረጥኸው ትጨምር ዘንድ እነሆ እሳትንና ውኃን አኖረልህ፤ ሕይወትና ሞትም በሰው ፊት ናቸው ከእነርሱም የመረጠውን ይሰጡታል” /ሲራ.15፡11-17/፤ “በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንድ በእግዚአብሔር ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል፡፡ ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው፤ ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፤ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም” /ዮሐ.3፡18-20/፡፡ የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ ከሌለው ለሚሠራው ሥራ ተጠያቂ አይሆንም፡፡ እንግዲያውስ እነዚህንና ተመሳሳይ አስረጂዎችን ይዘን እግዚአብሔር ሰዎችን አስቀድሞ ለጽድቅ ወይም ለኩነኔ ወስኖአቸዋል ከማለት እንጠበቅ፡፡

© ከ ዓምደ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊ መተግበሪያ የተወሰደ ፅሁፍ